# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ፕሮጀክቶች በአካባቢያዊ ደህንነትና ጥበቃ መነጽር ሲታዩ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሀገሪቱን የኃይል ፍላጎት ለማሳካት ከተለያዩ ታዳሽ የኃይል አማራጮች የኤሌክትሪክ ኃይልን በማምረት የሀገሪቱን ልማት በማፋጠን በኩል የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል። ተቋሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደረገ የመጣውን የኃይል ፍላጎት መመለስ እንዲያስችለው በርካታ የኃይል ማመንጫዎች፣ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች እና ማከፋፈያ ጣቢያዎችን ገንብቷል። አሁንም በመገንባት ላይ ይገኛል። እነዚህ የሚገነቡ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማቶች ከመገንባታቸው በፊት የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ይከናወናሉ። ለመሆኑ ከፕሮጀክቶች ግንባታ በፊት የሚከናወኑ ልዩ ልዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ምንድናቸው? የአተገባበር ሂደቱስ ምን ይመስላል? ለሚሉት ጥያቄዎች በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የአካባቢያዊ ደህንነትና ጤና ዳይሬክተር አቶ ታደሰ ብሩ የሰጡንን መረጃ አቅርበንላችኋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በኤሌክትሪክ ዘርፍ የሚገነቡ መሰረተ ልማቶች ከመገንባታቸው በፊት ከአካባቢያዊ ደህንነትና ጤና (environmental Safty & health)፣ ከኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትና ከማህበራዊ አገልግሎቶች አንፃር ይጠናሉ። ከወረዳ እስከ ክልል ካሉ የመስተዳድር አካላት፣ ከአካባቢው ነዋሪዎችና ባለድርሻዎች ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ተደርጎ ሃሳብ አስተያየት ይሰበሰባል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክቶችን ሲገነባ የአካባቢ፣ የጤና እና የደህንነት ተጽዕኖዎችን አስቀድሞ እየለየ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል። የተቋሙ የመጪው አስር ዓመት እቅድ እንደሚያመላክተውም ፕሮጀክቶች ከተጠቀሱት መስፈርቶች አንጻር በሚገባ እየተፈተሹ እና ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ የሚሰጡ መሆናቸው እየተረጋገጠ ወደ ሥራ ይገባል።

ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት በአዲስ መልክ



አቶ ታደሰ ብሩ

የተቋቋመው ይህ ዲፓርትመንት ጉዳዩን በተሻለ መልክ ለማሳለጥ ያስችለው ዘንድ የአካባቢ ጥበቃ እና የማህበረሰብ ጥበቃ ፖሊሲ አዘጋጅቷል። የተለያዩ አዋጆችን፤ ደንቦችን እንዲሁም ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዘ ያሉ ዓለም አቀፍ መመሪያዎችን እና መርሆዎችን መሰረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል። ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተናቦ የመሥራት ልምዱም እያደገ መጥቷል። ተቋሙ ገለልተኛ የሆኑ አማካሪዎችን በመቅጠር አካባቢ ላይ የሚደርሱ ተጽዕኖዎችን መቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን ይከተላል። ስለሆነም የሥራ ክፍሉ እቅድ ያወጣል፣ እቅዶችን ያስፈፅማል፤ ይገመግማል ክፍተቶች ካሉ የማስተካከያ ርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል ሲሌ አቶ ታደሰ ገልፀዋል።

የፕሮጀክቶች ግንባታ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ማስቀረት፣ ወይም መቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን የምንጊዜም ተግባር ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ፕሮጀክቱ በሚገነባበት አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ከአካባቢያቸው እንዲነሱ የሚያስገድዳቸው ነገር ሲኖር እንደሀገር በተቀመጠው ደንብና መመሪያ መሰረት የካሳና የመልሶ ማስፈር ሥራዎች ይከናወናሉ፤ እንደአስፈላጊነቱ የጤና፣ የትምህርት፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦት እና የሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑም ይደረጋል።

ፕሮጀክቱ በሚገነባባቸው አካባቢዎች ለሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ተጓዳኝ የሆኑ የልማት ሥራዎች የሚሠሩ መሆኑን ያወሱት አቶ ታደሰ፤ ለማሳያነት የወላይታ ኮንቨርተር ስቴሽን የተገነባበት ቦታ አርሶ አደሮች ለከብቶቻቸው ግጦሽ የሚጠቀሙበት ስለነበር፤ ከብቶቻቸው የምግብ እጥረት እንዳያጋጥማቸው የከብት መኖ ማቀነባበሪያ ግንባታ እየተገነባ እንዳለ አስታውሰዋል። በተጨማሪም የጊቤ III የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ውሃው የተኛበት ቦታ የዳውሮ ዞንና የወላይታ ዞን ነዋሪዎች የሚያደርጉት ማህበራዊ መስተጋብር እንዳይቋረጥ ተቋሙ ለአካባቢው ወጣቶች 11 (አስራ አንድ) ጀልባዎችን ገዝቶ በመስጠት የውሃ ላይ ትራንስፖርት እንዲኖርና የእርስ በርስ ግንኙነቱ እንዲቀጥል ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም የአካባቢው ማህበረሰብ በተለይም ወጣቶች በዓሳ እርባታ ላይ እንዲሰማሩም ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። በአካባቢው የሚገኙ ማህበረሰቦች፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማስቻል ተቋሙ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ተወጥቷል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በዋናነት ኃይል የሚያመነጨው ሀገሪቱ ካላት እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ከሆኑት ታዳሽ ኃይሎች ነው። እነዚህም የካርበን ልቀት መጠናቸው በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ዓለም ለአየር ንብረት ለውጥ እየሰጠ ያለውን ትኩረት በእጅጉ የሚደግፉ ናቸው።

ኢትዮጵያውያን ከአናናር ዘይቤያችን ጋር ተያይዞ ከፍተኛው የኃይል ምንጫችን ማገዶ ነው ያሉት አቶ ታደሰ፤ ይህም የደን መጨፍጨፍን ያስከትላል፤ የካርበን ልቀት መጠንንም ያሳድጋል ብለዋል።

ተቋሙ በአስር ዓመት መርሃ-ግብሩ የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን አሁን ካለበት ከፍ በማድረግ የህብረተሰቡን የአናናር ዘይቤ ከማገዶ ወደ ኤሌክትሪክ በመቀየር በአካባቢ ላይ የሚደርስ ተጽዕኖን የሚቀንስና አረንጓዳ ልማቱን የሚደግፍ ሥራ በመሥራት ላይ ይገኛል።

በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ከሆኑት ጉዳዮች ሌላው ትራንስፖርት ነው። መንግሥት በኤሌክትሪክ የሚሠሩ መኪኖችን ሥራ ላይ እንዲውሉ ማበረታታት መጀመሩን ተከትሎ ተቋሙ ኤሌክትሪክ ለዚህ ዓላማ እንዲውል እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

ከጤና እና ደህንነት አንጻር ሲታይ ኤሌክትሪክ በአግባቡ ካልተያዘ በሠራተኛውም ሆነ በተጠቃሚው ማህበረሰብ ላይም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። ማህበረሰቡ የተሻለ ንቃተ-ሕሊና እንዲኖረውና የተቋሙ ሠራተኞችም ደረጃቸውን የጠበቁ የደህንነት ቁሳቁስን እንዲያሟሉና ተገቢውን የአሠራር ሥርዓት እንዲከተሉ እየተደረገ ነው። ስለሆነም የውጭ እና የሀገር ውስጥ ኮንትራክተሮች ፕሮጀክቶችን በሚሠሩ ጊዜ በአካባቢያዊ ደህንነትና በጤና አጠባበቅ ልምድና እውቅና ያላቸው መሆኑ ይረጋገጣል። ከዚህ አንጻር ወደ ሥራ ሲገቡም ድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር ይካሄዳል። በአጠቃላይ ፕሮጀክቶች ከመነሻ ሃሳብ ጀምሮ ሥራ እስከሚጀምሩ ድረስ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖር የአካባቢያዊ ደህንነትና ጤና ስራዎች በጥናት የሚከናወኑ መሆኑን እንዲሁም በተገኘው ውጤት ላይ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር የሚተገበር መሆኑን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል